# አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ

እየታየና እየተሰማ ያለው ምንድር ነው? በአማራ ምድር የወያኔው ጠ/ሚር ተብዬ ባደባባይ ጦርነት በጎንደርና በጎጃም ላይ ሲያውጅ በሶሻል ሚዲያ ብዙ ተነብንቦለታል ነገርግን ሁሉም የሳቱትና ያላጋነኑት ጉዳይ አለ፡ ወደሁዋላ ሂዱና ቴፑን በደንብ ተከ ታተሉት፡ ሰውየው እንዲህ ማለቱን ትሰሙታላችሁ፡" 20 ሚሊዮን ሕዝብ ቢያምጽ ወይም ቢሄድ የሚጎዳን ነገር የለም"። አባባሉ አማራው እኛን ተቀብሎና ያልንውን በሞላ እሺ እያለ መኖር ካልፈለገ እኛም አንፈልገውም ቢፈልግ ገደል ይግባ የሚል ምንም የማያሻማ ምላሽ ነበር የሰጠው፡፡

በወቅቱ ለምን እሳትን ጨምሮ እቺን ክፉ አባባሉን እንዳለፉዋት ለኔ ባይገባኝም፡ አልፎ አልፎ ከስራ ጫና የተነሳ ባንዳንድ ክፉ የባለስልጣኖች አነጋገሮች ላይ ረጋ ያለና የሰከነ ትንታኔ የሚሰጥ ሰው ግን ከተቃዋሚዎች ጎራ እምብዛም አይቼ ስለ ማላውቅ ብዙም ያነሳሁት ነጥብ አነጋጋሪ እንዲሆን አልሻም። ወጣም ወረደ በሰ ውዬው የጦርነት አዋጅ አሁን እየታመሰ ያለው የጎንደርና ጎጃም ሕዝብ ስለሆነ በ ዛ ያለው የአማራ ታጋይ በምንም ዓይነት ወዳጁ ሊሆን ከማይችለው ብ አ ዴ ን ጋር ዕትብቱን በጥሶ ላንዴና ለመጨረሻ ግዜ መለያየት ይኖርበታል።

ምንም እንከዋን በዚህ ባንዳና ፈጽሞ ሊማርና ሊለወጥ በማይችል ስብስብ ውስጥ በርካታ የጎንደርና ጎጃም ልጆች ቢኖሩበትም ለዘራቸውና ለወገናቸው መቆርቆርና ማሰብ ካቆሙና አማራነታቸውን በመሸጥ ለወያኔ በማደራቸው የጎንደርና ጎጃም ደም በከንቱ እንዲፈስ ምክንያት ሆነዋል፡ ስለዚህ እነዚህን ትቢያዎች ያንተ ልጆች አለመሆናቸውን ሆድህ እንዲቆርጥልህ አሞትህን በማኮስተር በሚመችህ መንገድ ሁሉ ተጠቅመህ በዕለት ኑሮዋቸው ላይ ጫና በማሳደር ከጎንህ ገፍትረህ ገደል እን ዲገቡ ውሳኔ ላይ መድረስ ይኖርብሀል።

አማራው በሐምሌና ነሀሴ ወራት ተነስተህ ለለውጥ አደባባይ ላይ ብሶትህን ስታሰማ በጭካኔ ካጠገብህ የተነጠሉትን ልጆችህንና ቤተሰቦችህን ምንግዜም አትርሳ፡ አሁንም ወገኖችህ እየተገደሉብህና በጅምላ እየታፈሱብህ፤ በስልክና በመሳሰለው ከዘመዶችህ ጋር እንዳትገናኝ መብትህን ተነጥቀህና በድቅደቅ ጨለማ መብራት ተቆርጦብህ ያለው በማንነትህ ራስህን አውቀህ ሆ! ብለህ በመነሳትህና ወያኔ ደግሞ በጠ/ሚሩ አማካኝነት እንደነገረህ ኖርክም አልኖርክም የማይፈልግህ መሆኑን ተረዳና ጦር መዘህ እስከመጨ

ረሻው ተፋለመው።

የወያኔ ደጋፊና ሰላዮችን በጉያህ አቅፈህና ወገኖቼ ናቸው እያልክ ራስህን ማታለሉ ቢበቃህ ይሻላል፡ እነርሱ ባንተ ሞት፤ ባንተ መታሰርና ንብረትህ በእሳት ተቃጥሎ መጥፋት ቅንጣት ያህል አይሰማቸውም፤ አንተንም ወገናችን ነው ብለው ከመጤፍ አይቆጥሩህም። እነዚህን ነቀዞች ካጠገብህ ማስወገድና መቅጣት ይኖርብሀል፡ አለበ ለዚያ በሁለት ወራት ትግል ያፈሰስከው ደም ከንቱ ሆኖ ይቀርብሀል።

ከዚህ ክልል ከዛ ክልል በመጡ ወታደሮች እየተገደልን ነው የሚለውን አስተሳሰብ ተውና በወያኔ ዓላማ ተወጥሮ እየመታህ ያለው ወታደር ሁሉ ወያኔ ነው ብለህ መ ጋፈጥና ያለርህራሄ ካልመታህው በሆደ ሰፊነት የሚተርፍህ በሀዘን፤ በሰቆቃ፤ በባር ነትና እንደ ከብት እየተነዳህ መኖር ብቻ ይሆናል። ብ አ ዴ ንም፤ አጋዚም፤ ፌደራ ል ፖሊስም፤ የክልል ታጣቂዎችና የጸጥታ አባሎችም አንድ ላይ ሆነው በየቀኑ የቁ ም ስቅልህን እንደሚያሳዩህ ካንተ የበለጠ የሚያውቅ አይኖርም፡ ስለዚህ የዘረዘርኩ ዋቸው ሁሉ ጠላቶችህ ወያኔዎች መሆናቸውን ያለምንም ማወላወል አምነህ ታገላ ቸው።

ኢቢሲን ተወውና የአማራ ቲቪ የሚባለውን የሚያቅለሸልሽ ሚዲያ ጨክነህ ካደመ ጥከው በጎንደርና ጎጃም እንከዋን ሳይል "በክልሉ አንዳንድ አካባቢዎች. . ." በትም ክህተኞችና ከውጭ ሀይል ጋር ግንኙነት ባላቸው "የፀረ ሰላምና ፀረ ልማት" ሀይሎ ች የታገዙ "ፅንፈኞች " በንብረትና በህይወት ላይ ጉዳት አድርሰዋል የሚልና " በትግ ሬ ብሔረሰብ " ላይ ያነጣጠረ ጥፋት አድርገዋል ወዘተ. በሚል ሁኔታ ያንተን አማራ ነት ትግል አድበስብሶ አናሳና በጥላት የተለወሰ ዜና በየቀኑ እየነዛ ባለበት ባሁኑ ወቅት " መንግስት ስብሰባ ጠርቶዋል " እያልክ ገና ከስብሰባው ሳትወጣ ወገኖችህን ከሚያር ድ ሴጣን ጋር ተቀምጠህ የምታደርገው ውይይት የትም አያደርስህም፡ እንዲያውም የበለጠ የወያኔ ባሪያ እንደሚያደርግህ በጥሞና አስብበት፡ "እባብን ጭንቅላቱን ካል መታህ ነድፎ ይገልሀል ለስከንድ እንከዋን አያወላውልም፡ ወያኔም ከእባብ የማይለ ይ መሆኑን ማወቅ አለብህ።

በባህርዳር ያሉትን የወያኔ ተቅዋሞች በተለይም የቲቪና ኮሚዩኒኬሽን ጽ/ት ቤቶች ካገልግሎት ውጪ ማድረግ እጅጉን ለትግልህ ይጠቅምሀል በከንቱ ነገ ጠዋት ብ አ ዴ ን ካሳ ከፍሎ እንደገና ለዛውም በተሻለ ሆኔታ የሚያቋዋቁማቸውን የትግሬዎች

የንግድ መደብሮችን ስትመታ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን አብረህ ማስወገድ ይኖርብሀል። ቁልቁዋል እንኩዋን ራሱን ለመከላከል እሾክ ያበቅላል፡ ይህን ደግሞ ከቁልቁዋል አገ ር የመጡትና አሁን ቁም ስቅልህን እያሳዩህ ያሉት ወያኔዎችም በሚገባ ያውቁታል። ታዲያ አንተ አማራው እስከመቼ የእሳት ራት ሆነህ ትዘልቃለህ? እንደ እሳት ሆነህ ወያኔንና ቅጠሎቹን እንዲሁም ቅርንጫፎቹን ከነስራቸው የምታነደውና ከጫንቃህ ላይ የምታስወግደው መቼ ነው? መላው የወልቃይት አማራ ለተቀጣጠለው የአማራ ትግል ዋነኛ ምክንያት ስለሆነ የትጥቅ ትግሉን የምታግሉትና "ሰላማዊ ከምትሉትና" ምንም ውጤት ከማያመጣው መስመር የምትወጡት መቼ ነው?

እስቲ በየከተሞችና መንደሮች በወያኔ ጦር የሚሰቃየውን የጎንደርና ጎጃም አማራ በደ ንብ አድርጉና አስተውሉት፡ በየት/ት ቤቱ ከታሰረው ሌላ ከ 4 ሺህ የማያንስ በብር ሸ ለቆ የምዕራብ እዝ እስር ላይ ታጉሮ ቶርቸር እየተደረገ ስቃዩን በመቅመስ ላይ ይገኛል የወያኔው የአማራ ክልል ፕሮፓጋንዳ ሀላፊ ንጉሱ ጥላሁን በዚህ ጉዳይ ለቪኦኤ "ወጣ ቶቹ በብር ሸለቆ ከስህተታቸው እንዲማሩና እንዲመለሱ ስልጠና እየሰጠናቸው ስለሆ ነ ስልጠናው ሲያበቃ ተመልሰው ሕብረተሰቡን ይቀላቀላሉ፡ ይህንንም የምናደርገው ከቤተሰቦቻቸውና ወላጆቻቸው ጋር ተመካክረን በደረስንው ስምምነት ነው" ሲል አድ ምጠናል፡፡ ለኔ የሚገርመኝ ወያኔዎች በሙሉ ይሉንታ የሌላቸውና ፈጣሪን የማይፈሩ አጋንንቶች እንዴት ሊሆኑ እንደቻሉ ብቻ ነው፡ ወቼ ጉድ!!!
አብነት ሁነኛው ነኝ!